# አሁንም የድሮው ችግር ሲድበሰበስ
# ግልፅ ውይይት
# አስተያየትና የመፍትሔ ሃሳቦች

ከ ቀለሙ ሰሜነህ አፕሪል/ሚያዝያ 2007/1999ዓ.ም

I

## መግቢያ

ይህችን ጽሁፍ ስጀምር ብዙም ለማለት አልከጀልኩም ነበር። የነገሩ ክብደትና ጥልቀት ግን በዋዛ አልለቀቀኝም። ስለዚህም ሳትሰላቹ እንድታነቡኝ እጠይቃለሁ።

ሰሞኑንን ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሰለተቃዋሚው ዳያስፖራ ፖለቲካ አስተዋጽኦ ደጋግመው ጽፈዋል። መልካም ጅምር ነው። ከንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ አዋንታዊ ለውጥ ሊመጣ የሚችለው በውይይትና በሰላማዊ መንገድ፣ በመግባባት በ "እነካ -ስጠኝ" ነው። ጥላቻና መናናቅ ላነዴና ለሁሌም መቅረት አለበት። የኋላ-ቀርነት፣ የ እውቀት ማነስ ምልክት ነውና!

...................

ካለፈው የ ኢትዮጵያ አገራዊ ምርጫ ወዲህ ሃሳቤን በ አመክሮ ለመግለፅ ስሞክር ይህ የመጀመርያ ጊዜየ ነው። ነገሩን አዙሬ አገላብጬ አየሁትና ዋናው መሰረቱ በዚህ ፅሁፍ ላይ ያሰፈርኩት ሆኖ አገኘሁት። እነሆ ሁላችንም በሚገባን ቋንቋ ከዚህ በታች እዘረዝረዋለሁ። ብዙ የ እንግሊዝኛ ቋንቋ የሚከብዳቸው ወይም የማይችሉ ወገኖቻችን አሉና እነሱን ለማግኘት ስል አማርኛን መርጫለሁ; ለብዙ ጊዜ እጄ (አይምሮዬም) የተለማመደው የንግሊዝኛ ጽሁፍ ዘይቤውን ስለሆነ አንባቢው ይህንን ችግሬን አውቆልኝ በጎደለው እያሟላ እነዲያነበው እጠይቃለሁኝ።

ሌላም የምለው አለኝ። አነሳሴ እውነቱን ለማሳወቅ ብቻ ነው። ምንድነው እነዲህ የሚያበጣብጠን ብሎ ሁሉም ራሱን እንዲጠይቅ እፈልጋለሁ። በመሃከላችን ብዙ ወጣቶች ወደ ፖለቲካው እያተኮሩ ያሉ አሉ። ሁሉንም ነገር ሳያዩት፡ ያለፈ ያገራቸውን ታሪክ ሳያውቁ በዳያስፖራ ፖለቲካ ውስጥ በጭፍን እንዳይገቡ ከሁላችንም የምናውቀውን ያክል እንድናካፍል አገራዊ ግዴታ አለብን። ይህም አነዱ ዓላማዬ ነው። በዚህ ጉዞየ አላሰፈላጊ ቃላት ከተጠቀምኩኝ ሰውን ለማስቀየም ብየ እንዳልሆነ አንባቢው እንዲረዳልኝ እፈልጋለሁ።

..................

በዚህ ጽሁፌ አንድ እርምጃ ወደ ኋላ በመሄድ የተረሳ ወይም የተድበሰበሰ የመሰለኝን ትልቅ ችግር ማንሳት እወዳለሁኝ። የዲያስፖራው ፖለቲካ ለምን ይህ አሁን የያዘውን የጥላቻ መልክ ያዘ ለሚለው ጥያቄ በመጠኑም ቢሆን መልስ ይሆናል ብየ እገምታለሁኝ።

መካረሩ፣ መጠላላቱ፣ መፎካከሩ የበዛው በ ኤኮኖሚው፣ በዲሞክራሲያዊ አስተዳደር፤ በሰዎች አጠቃላይ መብት አተረጓገም ቅራኔ ወይም ልዩነት ስላለ አይደለም። ይህ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

መኖር የሚገባው፣ ሁሉም አገር ያለ ነገር ነውና። ወይም ያለው መንግስት ፀረ-ኢትዮጵያ ስለሆነ አይደለም። እንደዚያ አድርጎ ማሰብ ከኛ የበለጠ ኢትዮጵያዊ የለም ማለትን ያስከትላልና። እንዲህም ማለት ግብዝነት ነውና። ዋናው የነበረውና ያለው ችግር የብሄር ጥያቄ አፈታት ላይ ነው። **ይህንን ከካድን ዋና በሽታችንን ካድን ማለት ነውና ይህ እስከሆነ ድረስ ለበሽታችን ምንም አይነት መፍትሄ ማግኘት ዘበት ይሆንብናል።**

'ጎሰኛነት'፣ የሚጠፋው ጎሳዎቹ በ እኩልነት መታየታቸውን ሲያረጋግጡ ነው፡ የሃይማኖት መካረሩ የሚጠፋው ሃይማኖቶች ሁሉ ያላድለዎና ንቀት ተቀባይነት እንዳላቸው አማኞቹ መተማመኛ ሲያገኙ ነው። ስለዚህ ጎሰኝነት የሚጠፋው 'ጎሰኛው' ያነሳውን ጥያቄ ስናነሳና መፍትሂውን ስንሻ፣ 'አክራሪው' ያነሳውን ችግር ስንመረምርና ሲገባን ስለዚህም ሁላችንም ስንግባባ እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። መከባበርና መግባባት የሚመጣው ደግሞ ያገሪቱ ህግ ለሁሉም እኩል ሆኖ ሲያገለግል ነው።

ይህ ሲባል ሌሎች ችግሮቻችን በቀላሉ ይታያሉ ማለት አይደለም። ገና ጀማሪዎች ስለሆንን ጨዋ የሆነ የፖለቲካ ልዩነት አፈታት ልምድና ባህል የለንም። ሓይል ይቀድማል። ትናንሽ ችግሮች ሥር እየሰደዱ መጥተው ትላልቅ ሆነዋል። ስለዚህም ትኩረት ተሰጥቷቸው መፈታት ያለባቸው ችግሮቻችን እንደሆኑ እንገነዘባለን።

------------------

## ዓላማው፡- ለምን አስፈለገ?

የዚህ ጽሁፍ ዋና ዓላማ ስለተነሳው ርእስ ላንባቢዎች ትምህርት ወይም ግንዛቤ ለመስጠት አየደለም። ሰለብሔር ጥያቄ ተደጋግሞ የተባለ ስለሆነ ሁላችንም መጠነኛ እውቀት ይኖረናል። ዋናው አላማ ተቃዋሚ ሃይሉ መሠረታዊ የልዩነት ነጥቡ እነዲጠራ ለማድረግ ነው፣ ይህ አሁን ተደበላልቆ ያለውን አገራዊ ፖለቲካ አጀንዳና የጥላቻ  ፖለቲከኞችን አካሄድ አንባቢው ጠልቆ እንዲረዳው አስተዋጽኦ ለማደረግ ነው። ትክክለኛውን የትግል ዘዴ ይዘው ለፍትሃዊ አስተዳደር የሚታገሉትን ፓርቲዎች መርዳት የምንችለው ማን ምን እንደሆነ መለየቱ ላይ የምናውቀውን ስናካፍል ነው። ለፍትህና ለርትዕ፣ ለተሻለ አስተዳደር በስላማዊና ጨዋ (ሲቪል) መንገድ የሚታገሉት አገር በቀል ፓርቲዎች የ አክራሪዎች ሆሆታና ጩኸት በዝቶባቸው አንገታቸውን እሰከመድፋት የደረሱበት ጊዜ ላይ ያለን ይመስለኛል። በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ በጩኸቱ ተደናግጠው ህሊናቸው የሚነግራቸውን ትክለኛውን ነገር ለማደረግ እጃቸውን ሲይዛቸው እንመለከታለን።ባሁኑ ጊዜ ከውውይት ይልቅ ጩኸቱ ስለበረከተ ገለባው ገዝፎ ጥሬው የታመቀበት ደረጃ ላይ እንገኛለን። በዚሁ ከቀጠልን ላገራችን የምናደርገው አስተዋጽኦ እጅግ አናሳ ከመሆኑም በላይ ቢኖርም አሉታዊ ነው።

…………………..



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

## ከትግል ታሪካችን በትንሹ

ካንድ ወዳጄ ጋር ስንጨዋወት ያለፍንበትን የትግል ታሪክ ሳናነሳ በድፍኑ ውይይት መጀመር አስታማሪነቱ ጎዶሎ ይሆናል ሰላለኝ ከብዙ በጥቂቱ አንባቢ ያለፈውን እነዲዘክር ትንሽ ልበል። ስለ ኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቀስቃሴ በበለጠ ለመረዳት የሚፈልግ ሰው የ ፈንታሁን ጥሩነህን መጻፍ "The Ethiopian Students: Their Struggle to Articulate the Ethiopian Revolution -1990" እነዲያነብ ልጠቅም እፈልጋለሁ።

የ ኢትዮጵያ ግራ-ዘንበል አሰተሳሰብ በተደራጀ መልኩ የጀመረው በ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በመጀመርያ 1950 ዎቹ ገና የ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ (ያሁኑ ዩኒቨርሲቲ) በተቋቋመበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል። ያኔ ገና ተማሪዎቹ የጀነራል መንግሰቱ ንዋይን መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሲደግፉ። ብዙም ሳይቆይ በየካቲት 1957 ኢ.ም **የመሬት ላራሹ** ጥያቄ ተነሳ። ይህ የ መጀመሪያው የኢትዮጵያ ስር ነቀል ህበረተሰባዊ (ሶሻል) አብዮት ጥነስስ ነበር ማለት ይቻላል። ይህ አቋምና ጥያቄ ከማንኛውም ይልቅ የ ደቡባዊ ኢትዮጵያን ጥያቄ የሚያነጸባርቅ አዲስ ጅምር ነበር።

የዩኒቨርሲቲውና ባጠቃላይም የተማሪው ክፍል ድርጅታዊ አቋሙን ሲያጠናክር ቆይቶ፣ በ1962 ዓ.ም የጥላሁን ግዛው መመረጥና እሱን ተከትሎ የ ታዋቂው ዋለልኝ መኮነን የብሄሮች ጥያቄ ትንታኔና አቋም ሁለቱን መሰረታዊ የኢትዮጵያ ጥያቄዎች **-የመሬት ላራሹ ጥያቄና የብሄሮች ጭቆና ጥያቄ** ለመጀመርያ ጊዜ ስር ሰደው ዋናነት ያዙ።

አንባቢው ሊያስተውለው የሚገባ ነገር ቢኖር እነ ዋለልኝም ሆኑ ሌሎች ታጋዮች የመሬትንና የብሄር ጥያቄን ሲቀበሉ ከስሜት ተነስተው አይደለም። የ1940ዎቹ የቀድሞው ወያነ አመጽ በትግራይ፣ የባሌ እነቅስቃሴ በጠቃላይ የመጫ-ቱለማ እንቅስቃሴ በ ኦሮምያ ጎልተው ከሚታዩት የህዝብ እንቅስቃሴዎች ዋነኞቹ ናቸው።

ሁኔታዎች በጣም በፍጥነት የሚጓዙበትና 'ግራውና ቀኙ' ፖለቲካ አስተሳሰብ ጎልቶ መውጣት የጀመረበት ጊዜ ነበር። ጥላሁን ግዛው ካንድ አመት በፊት በመኮንን ቢሻው (ቢኋላ ዶር መኮንን - ነፍሳቸውን ይማረውና አሁን በቅርቡ በሞት የተለዩን) ተሸንፎ አሁን መሪነቱን የያዘው የግራ መስመሩን አካሮ ገፋው። በዚህም የተነሳ ስለጣኑን የጨበጡት የገዛ ዘመዶቹ ባንዲት ምሽት ረሸኑት። የማያውቅ አንባቢ ካለ ጥላሁን ግዛው የንጉሰ ነገሥቱ ልጅ የ ልዑል መኮንን ባለቤት ወንድም ነበር።

የተማሪው እንቅስቃሴ ግን እየተጠናከረ መጣ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለዘልዓለም ስማቸው የማይረሳው የንቅስቃሰው መሪዎች **ከስመ-ጥሩው ታጋይና መሪ ብረሃነመስቀል ረዳ** ጋር ሆነው ለስርዓቱ ያላቸውን ተቃውሞ በግልጽ ለ ዓለም በማሳየት የኢትዮጵያን አይሮፕላን በመጥለፍ አገር ለቀው ሄዱ። የ ዓመጻ ትግሉ ተጀመረ። ፋኖው ተሰማራ!!



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

(እዚህ የብርሃነ መስቀልንና ጓዶቹን ስም እንደዋዛ አንስቼ አልፌዋለሁ። አቶ ብረሃነመስቀል አነዳንድ የድሮ ተቃናቃኞቹ እንደጻፉት ሳይሆን በጣም ብልህ፣ አዋቂና ባስተሳሰቡ ጥራት (ክላሪቲ) የነበረው ሰው መሆኑን አጥብቀው የሚያውቁት በህይወት ያሉ ሰዎች ይናገራሉ። ጊዜው ሲፈቅድና ሲያመቻቻው የነበሩት የእውነት መልዕክተኞች እውነቱን እስኪነግሩን ድረስ እንግዲህ መጠበቅ ነው።)

በዚህ ጊዜ ነበር አገራዊ የሆነ የሰርቶ-አደር/ላባደር ትግል ነው የሚሻለው ወይስ የብሔር ትግል ነው የሚበጀው የሚል ጥያቄ ማንሰራራት የጀመረው። ባንድ በኩል አብዛኛውን  የ ኢትዮጵያ ተማሪዎች ያቀፈው ቡድን በመነጣጠል ትግሉን ከመግፋት ይልቅ ባንድነት ብንነሳና ብንታገል አገሪቱን ባፋጣኝ ነፃ እናደርጋተለን ሲል ሌላኛው አነስተኛው ቡድን ደግሞ መደራጀት የሚቀለው በብሄር ሲሆን ነው የሚለው በሌላ ሆነው ክርክሩ ይካሄድ ነበር። በብሄር ጀምረን ኋላ አንድነት እንመስርት የሚለው በዚያን ጊዜ ከስተራተጂክ ጥያቄ ይልቅ የታክቲክ ጥያቄ ሆኖ ባብዛኘው ይቀርብ ነበር። በተለይ የ ህወሓት (ቲፒኤልአፍ) አስተሳብ እሰከመጨረሻው ድረስ ይህን አቋም አቀንቅኖ ነበር የተጓዘው። ሁዋላም በኢህአዴግ የተመራው የ ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሥርዓትም ይህንን አቋም ነው ያነጻባረቀው።

ባጠቃላይ የተማሪው ማህበራት የ ኢትዮጵያን የብሄሮች ጥያቄ ማስተጋባት ጀመሩ። የብሄርና የመሬት ጥያቄ -በተለይ በደቡባችን የማይገነጣጠሉ ጥያቄዎች ናቸው ተባለ። “የብሄሮች መብት እስከመገንጠል ድረስ” የሚባለው አቋም የዋነኛውና የብዙሓኑ የ ኢትዮጵያ አብዮታዊ እንቅስቃሴ አቋም ሆነ ። አሁን በብዛት የሚኮነነውና ኢህአዴግ በሕገ-መንግስቱ ‘አንቀጽ 39’ ያካተተው የዜጎች መብት ያኔ የሁላችን አቋም የነበረ መሆኑን መረዳት መፍትሂ ለማግኘት ለምናደርገው ሙከራ ግንዛቤ ይሰጠናል ብየ አስባለሁ።

እዚህ ላይ አንባቢው በሚገባ ሊገነዘበው የሚገባው ነገር የብሄር ጭቆናን አስመልክቶ ሲካሄድ፣ ሲቀነቀን የነበረው አሰተያየት ከማነኛውም ወገን ቢሆን የነገሩን አሳሳቢነት የሚያነጸባርቅ ነበር። ማንም ቢሆን አሁን እንደምንሰማው የብሄር ጭቆና አልነበረም የሚል እዚህ ግባ የሚባል ተቃዋሚ ሃሳብ አልተስተዋለም። ሌላው ቀርቶ ክፉው የደርግ መነግሥት ሳይቀር የብሄሮችን ጭቆና ተቀብሎ የራሱ መፍትሂ ለመስጠት ፕሮግራም አወጥቶ ይነቀሳቀስ ነበር።

ሁኔታዎች ይቀያየራሉ ግን መስመራቸውን፣ ያለፈውን እውን ታሪክ አይሽሩም። ያኔ የነበረው እንቅስቃሴ ስሜታዊነት የበዛበት ተመክሮ ያልነበረው፣ በወጣትነት የችኩልነት ጠባይ፣ አርቆ አለማሰብ ጉድለት፣ ወዘተ.. የተነሳ ብዙ ስህተቶችን የሰራ እንቅስቃሴ ነበር። ግን ባንድ ነገር አይታማም። ይኸውም የጭቆናውን ዓይነትና መጠን ያላንዳች ክህደት አሳምሮ ያስተጋባና ያሰተዋወቀ ትውልድ ነበር።

አሁን ታድያ የመደብና ያስተዳደግ ጉዳይ ሆነና አንዳንድ በድሮው ጊዜ በግንባር ቀደምትነት ትግሉን ሊመሩ ሲከጅሉ የነበሩ ሳይቀሩ ዘርና ፊውዳላዊ አስተዳደጋቸው፣ ‘አንቱ በሉን’ ባይነታቸው አሸንፏቸው አጥፊ ሚና ሲጫወቱ እያየናቸው ነው። ያስታርቃሉ ያልናቸው ሲያጣሉ፣ ይባስ ብለው እሳት ሲጭሩ በሃዘኔታ እያስተዋልናቸው ነው።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

*እንዳው ለነገሩ ለመሆኑ ያኔ 'የብሀሮች መብት እስከመገንጠል ድረስ' ብሎ ሲያስተጋባ የነበረው የብዙሓኑ ቡድን ስልጣን ቢይዝ ኖሮ ከ ኢህአደግ የተለየ አቋም ዪኖረው ነበርን? ያኔ የነበሩትና አሁን በህይወት ያሉት ይህንን ጥያቄ ራሳቸውን ሲጠይቁ ምን ይሰማቸው ይሆን?*

..................

***<u>አሁንስ የት ነው ያለነው?</u>***

*ይህ ያሁኑ የ ኢትዮጵያ አስተዳደር/ መንግሥት ባገር ከፋፋዪነት፤ በገነጣጣይነት ይታማል። ዕውነትነት አለው? ይህ ጥያቄ ወሳኝነት ያለው ጉዳይ ነውና ሳይበዛ ባጭሩ የሚገባኝን ያክል ለማካፈል እፈልጋለሁ። በርግጥ ሌሎች የጋራ የሆኑ ችግሮች (ህግ መከበር፡ መልካም አስተዳደር፣ዲሞክራሲ፤ ኢኮኖሚ ወዘተ.. የመሳሰሉ ሌሎች አጀንዳዎች - ሁለ-ገብ (ዩኒቨረሳል) የሆኑ የጋራ አጀንዳዎችን - የከፋፋይነት ባህሪ ሰለሌላቸው በዚህ ጽሁፌ አላነሳም። ጊዜና ቦታ ሲያገጣጥም በሰፊው ለወደፊቱ የምንወያይባቸው ጉዳዮች ናቸው።*

..................

*የ ኢሓደግን መንግሥት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ቅራኔ አፈታት አኳያ፤ ከ ኤርትራ ጥያቄ አፈታት አንጻር፤ የሰውን ሃሳብ ከመቀበል ድክመት አኳያ የምንቃወመው፣ ከኤኮኖሚ ዕድገትና ፖሊሲ፣ ካጠቃላይ አሰተዳደር አንጻር ደግሞ የምንደግፈው እንዳለን ሁሉ ሙሉ በሙሉ ይህንን መንግስት የሚኮንኑ የህዝብ ክፍሎች መኖራቸውን እንገነዘባለን። በተለይ በውጬ አለም። ባንጻሩ ደግሞ ያለውን ገዢ ፓርቲ ከነስህተቶቹ የሚደግፉት አሉ። ይልቁንም በጥላቻ ረድፍ ላይ የተሰለፉትን ስንመለከት ዋናው መንስኤ በዚህ ጽሁፍ ላይ የሰፈረው ነጥብ ነው ብየ አምናለሁ።*

......................

*ስለዚህ መንግሥት ከፋፋይነት ተደጋግመው የሚነሱት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።*

1) *አገሪቱን በብሄር (አክራሪዎች ጎሳ ይሉታል) የሚከፋፍል ፈደራሊስት አገዛዘ መሰረተ።*
    - *በዚህም የተነሳ ያንዱ ብሄር ተወላጅ ሌላ ክልል ዉስዋ ሄዶ መስራት አልቻለም፤ መድልዎ ይደረግበታል ወይም ለመድልዎ በር ከፈቷል*
    - *አለመተማመንንና መጠራጠርን ፈጥሯል፤*
    - *ለወደፊቱ አንዲት ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትገነባ የሚያደርግ ደነቃራ አስተዳደር ነው፡*

2) *ለተወሰኑ ክልሎች አድልዎ ያደርጋል*

*የሚሉ ናቸው።*

*የኢሕአዴግ መንግሥት እነዚህን ተቃዋሚ ሃሳቦች አሌ ዪላል።በተለይም፦*

1) *ዋናው የ ኢትዮጵያ ችግር የነበረው የብሔር ጭቆና ነው ስለዚህም ዋናው መፍትሄ ብሄሮችን ማጎልበት (ኢመፖውርምንት) ነው፡*
2) *ብሄር/ብሄረሰቦችን ማጎልብት መከፋፈልን ሳይሆን በኩልነት የተመሰረተ አንድነትን ነው የሚያመጣው ብሎ ይከራከራል።*
3) *ለተወሰኑ ክልሎች መድልዎ አይደረግም - ለተጎዱት ግን ማስተካከያ ድጎማ (ኢኳላይዘሽን) ፕሮግራም አለን ይላል።*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሓቁ ወይም እውነቱ የት ላይ ነው? አንዳንዴ ሃቁ እንደተመለካቹ እንደሚለያይ ብገነዘብም እኔና እንደኔ የሚያስቡት እንደምናየው ለማቅረብ እሞክራለሁኝ።

እዚህ ለይ ልዩነቶቹ እነዚህ ብቻ ከሆኑ ለምንድነው ጦር የሚያማዝዝ ያክል ልዩነትና የጠላትንት ስሜት የሚሰተዋለው? በተለይ በውጬ አለም ባሉ ኢትዮጵያውያን መካከል? ብሎ የሚጠይቅ ሰው በብዛት ይኖራል ብየ አስባልሁ። ዕውነትም እንቆቅልሹ እዚህ ላይ ነው። መደምደሚያው ላይ ልመለስበት እሞከራለሁ።

**II**

<u>የብሔር ጥያቄ ነበር ወይስ አልነበረም?</u>

ለመናገር ያህል ብዙ የዚህ ርዕስ ተተቺዎች የብሂሮችን እኩልነት ማን ካደና ነው ስለዚህ ነገር የሚጻፈው ብለው እነደሚተቹ አስቀድሜ እገነዘባለሁኝ። እንዳው ለይስሙላ መናገርና ማመን ለየቅሉ ናቸው። ተሸፋፍኖ ቀረበ እንጂ ዋናው የዲያስፖራ የፖለቲካ ተቃውሞ ኢህአደግ ለምን ክልል ፈጠረ፣ የብሂሮችን መብት የሚደነግግ ህግ በ ህገ-መንግሥቱ አካተተ ከሚል የተነሳ ነው። ይልቁንስ መካዱንና ማስመሰሉን ትቶ፣ በሽታን አውቆ ስለሆነ ለሁላችንም ሕዳሴና አዲስ ያንድነት ጉዞ የሚያስጀምረን ለራሳችን ስንል የእውነትን መንገድ እንያዝ።

እናም ትልቁ ጥያቄ ይህ ነው። ኢሕአዴግ የብሂርን ጥያቄ እንዴት ፈታው ወይም ሊፈታው ሞከረ የሚለው ነገር ሊያከራክረን ይችላል። ኢህአደግ ተጨባጭ ክልል በመቀየስ (ፊዚካል ዲማርኬሽን) ፈታሁት ይላል ከቅን ልቦና ተነስተው የሚቃወሙት ደግሞ ክልሉ ተጨባጭ ከመሆን ይልቅ ግንዛቢያዊ (ቨርቿል) ሊሆን ይገባዋል ይሉታል። ትልቁ ፈተና ግን ላይ የቀረበውን ጥያቄ-የብሂሮች የቆየ ጥያቄ-መመለሱ ላይ ነው።

…………………

ግልጽና ክፍት በሆነ አይምሮ ለተመለከተው ጥያቄው ከባድ አይደለም። ነገሩን ከሁለት አቅጣጫ በመምጣት ማየት ይቻላል። አንደኛው አቅጣጫ የተከለሉት ብሂረ-ሰቦች ስለመከለላቸው የራሳቸው አመለካከት እንዴት እነደሆነ መመልከት ሲሆን፤ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ከክልሉ ውጭ የሆኑ ህዘቦች ከጥቅማቸው አኳያ ማየቱ ነው።

……………………

ይህ በጣም አስፈላጊ ግንዛቤ ነው። ነገሮች ተደጋግመው ስለተነገሩ ብቻ እውነትነት አላቸው ማለት አይደለም። ለምሳሌ ከጥቂት አመታት በፊት በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚመራው የኢትዮጵያ ኤኮኖሚክ ጥናት ድርጅት የገጠሩን መሬት ሰሪት አስመልክቶ ጥናት አካሂዶ ነበር። ያኔ አብዛኛው ገበሬ አሁን ባለው ሰሪት ከሞላ-ጎደል የሚስማማ እነደሆነ ነበር ያሳየው ጥናቱ። ያገራችን ምሁር ግን ቀን ተሌት የመሬት ስሪቱ መቀየሩ ግዴታ ነው እያለ ይጽፋል። እነግዲህ ጥናቱ ጎዶሎ ነው ብሎ መከራከር ይቻል ይሆናል። ሆኖም ግን እስካሁን ድረስ የዚያን ጥናት ብክነት የሚያሳይ ሌላ ነገር (መረጃ) አላየሁም።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ወደ ዋናው ነጥባችን እንመለስና የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንመልከት፦

**ሀ) አሁን በክልል ተደራጅተው የሚገኙት ሕዘቦች አከላሉን -ከብሄር መብት አኳያ እንዴት ያዩታል?**
**ለ) ይህን አከላለል ተቃውመው የሚነሱ ብሄረ-ሰቦች ካሉ እስካሁን ድረስ ተቋውሟቸውን ያሰሙበት ሁኔታ አለ?**

-----------------

እኔ እስከማውቀው ድረስ በብሄር በመከለላቸው ምክንያት ተቃውሞ ያሰሙ ህዘቦች አልተመለከትኩም። እንዳውም ባነፃሩ **የክልሉ ዋና መገለጫ በሆነው በቋነቋና ባህል መከበር ደስተኞች መሆናቸውን ነው የምንገነዘበው።** ተቃውሞ ቢኖር የብሄር-ብሄረሰብ መበታችን ያለመገንጠል የሚታሰብ (የተሟላ) አይደለም ከሚሉት ነው (ለምሳሌ ኦነግ ና ሶማሌ ነፃ -አውጪ ግንባር)።

ይህ የብሄረ-ሰቦች መብት መከበር ጉዳይ - ካሁን በፊት የመብት ረገጣ - (ቢያንስ የብሄረ-ሰቦች ባህልና ቋንቋ ረገጣ) እነደነበር ያሳያል።

እዚህ ላይ ቋንቋና ባህል ለማከበር የብሄር ክልል ግዴታ ነወይ የሚል ጨዋ ጥያቄ መነሳቱ ትክክል ነው። ኋላ እንመለስበታለን።

ከሁሉም በፊት ግን አንድ ነገር አስተውለን እንለፍ። አንድ የህበረተሰብ አካል ወይም ግለሰብ የሚሰማኝ ይህ ነው ብሎ ሲነግረን -አይ! ተሳስተሃል እንደዚያ አልተሰማህም ብሎ መተነበይ አይቻልም። ሲሆን-ሲሆን ለምን እነዲህ አይነት ስሜት ተሰማው ብሎ አብሮ መፍትሂውን መፈለግ ካልተቻለ ደግሞ ደጉን መመኘት ነው።

የምንገነዘበው የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች ሰዎች ቋነቋና ባህላቸው በመከበሩ ምክንያት ደስ መሰኘታቸውን ነው። ይህ የመብት መከበር እውን የሚሆነው ደግሞ በቦታና ጊዜ (ታይም ና ሰፔስ) -ክልል ነው። ይህ ትክክለኛና ዋና ግንዛቤ ነውና ስሜታዊነት ባልበረዘው መንገድ ሊታይ ይገባል።

አይ! ህዝቦቹ ራሳቸው በቋንቋ - ባህል አነጻር መከለላቸውን ተቃውመዋል የሚል አሳማኝ መረጃ ከቀረበልኝ ከላይ ያልኩት ትክክል አይሆንምና አካሄዴን አስተካክላለሁ።

እኔ አውቅልሃለሁኝ ማለቱ ይቅር ለማለት ያክል ነው።

----------------------

የብሔር ጥያቄ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለውን **ለመመለስ ሌላኛው መንገድ ታሪክን መለስ በሎ መመልከት ነው።** በተለይ ወጣቱ ትውልድ የነበረውን ጭብጥ ታሪክ እንዲያውቅ የማድረግ ግዴታ በኛ ትንሽ በዕድሜ በገፋነው ጫንቃ ላይ ወድቋል።ግዴታችንን የምንወጣው ያለፈውን እውነት በምስክርነት ላዲሱ ትውልድ ስናስተላልፍ ነው። መጥፎ ታሪካችን እንደገና እነዳያንሰራራ ይረዳልና።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የድሮ ገገሮዎች ገገርነታቸውን ለማረጋገጥ፡ ሃይላቸውን ለማሳየት ሲሉ ከመንግሥት ትዕዛዝ ያፈነገጡትን ሰዎች መቀጣጫ እንዲሆኑ ፊታቸው በማረሻ እንዲተኮስ አድርገዋል።በዚህም ተግባራቸው የከረረ የጥላቻ መርዝ በትነዋል። ባንዳንድ ክልል ህዝቦች መሬታቸው ላይ ቀላድ እንዲጣል አድርገዋል (መሬት አልባ ገባር ሆነዋል)። ይህ ጉዳቱ ከደረሰባቸው አዛውንት አያቶችና ቅድመ-አያቶች የሰማሁትና ያየሁት፣ ይዞታውንም ራሴ የተመለከትኩት ነው። ተረት ተረት ወይም የይስሙላ ወሬ አይደለም።

ያየነው (ያየሁት) ሰዎች ያለቋነቋቸው ሲዳኙ ነው። እድለኞች ከሆኑ አስተርጓሚ ይመደብላቸው ነበር። ያማርኛ ቋንቋ ፈተና ካላለፉ የከፍተኛ ትምህርት እድል ሲነፈጋቸው ማየታችን ነው ሁላችንም አሌ ለማለት የሚያዳግተን ታሪክ። አዎን! የዛሬውና የነገው ትውልድ ሊያውቀው የሚገባ ነገር ቢኖር ከትላንት ወዲያ የነበሩ ወጣቶች - በሌላ የትምህርት ዓይነቶች ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ወጣቶች - አማርኛን በሚገባ ባለማለፋቸው ብቻ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ይነፈጋቸው እንደነበር ነው። የመሃል አገር ሰዎች -ሰሜናውያኑ ኤርትራውያን ሳይቀሩ መሬታቸውን ሲወስዱባቸው ነው (የተበዳዮቹን)። ባህላቸው ሲንቋሸሽና ሲጥላላ ነው። ይህ ዕውነታ ነው። ከዕውነታውም በጣም ትንሹ። ፋክት ይሉታል እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች። በነዚህ እውነታዎች የተነሳ -ተጨባጭና ዓይምሯዊ (ሳይኮሎጂያዊ) በሆነ መንገድ የተጎዱ ህዝቦች ነበሩ።

ይህንን መሠረት አድርገው ነው የብሄር እንቅስቃሴዎች ኢትዮጵያ ውስጥ የተስፋፉትና መጨረሻም አሸናፊ የሆኑት። በርግጥ የኤርትራው ሁኔታ ሌላ ገፅታ (ዳይመንሽን) እንደነበረው አስተውለን እናልፋለን። የራሱ ጣጣ አለውና እዚያ ውስጥ ገብቼ ያንባቢን ጊዜ ማባከን አልሻም።

ይህንን ሃቅ ተቀብለን ከተጓዝን የተቀረው መንገድ ጨርቅ ይሆንልናል።

----------------------------

**III**

## የብሄር-ክልል አስተዳደርና ችግሮቹ

ያለብንን ችግር ማወቅ ማለት መፍትሄውን ለማግኘት ከግማሽ መንገድ በላይ አብረን ተጉዘናል ማለት ነውና ከዚህ በኋላ ያለው ውይይታችን እስከዚህም ያከራክረናል ብየ አላምንም።

ትልቁ የ ኢትዮጵያ ችግር አገራችን ሁሉንም እኩል ታሰተናግድ ነበር፣ የብሄር ጭቆና የሚባል ነገር አልነበረም፣ ይህ የከፋፋዮችና የፀረ-ኢትዮጵያ ሴራ ነው፣ ወዘተ.. በማለት በ ኢትዮጵያዊነት ስም ጥላቻን የሚያስተናግዱት ናቸው። ችግሩ ከታመነ ግን ወደፊት አብሮ ከመገስገስ የሚያግደን ነገር አይኖርም። በነገራችን ላይ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸውን ወገኖቻችንን ማግባባት አንዱ ተግባራችን



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ከመሆኑ ጋራ አያይዞም ይህ አመለካከታቸው በ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውሰጥ አስተዋጽኦው አሉታዊ መሆኑን የመንገር ግዴታ አለብን ብየ አምናለሁኝ።

…………

ለምሳሌ አስተውሎ ላየው ቅንጅት የተባለው ደርጅት ለ1997 ምርጫ በ1997 ዓ.ም ሲመሰረት አንዱና ዋናው መለኪያው በብሄር የተደራጁ ፓርቲዎችን በውስጡ አለማስተናገድ ነበር። አፍራሽ'ንጂ ገንቢ አድርጎ ሰላላያቸው። ይህ ድርጅት የብሄሮችን ጥያቄ በቀጥታ ባይቀበልም ችግሩ እንዳለ ሳይገነዘበው አልቀረም።

……………..

እንመለስበታለን ብለን ያለፍነው ነገር ነበር። የብሄር ጭቆና ነበር ሲባል ጨቋኝ ብሄር ነበር ማለትን፣ በዚህ የተነሳ ያነድ ብሄር ከሌላው የበለጠ ጥቅም ማግኘትን አያመለክትም። ተጠቃሚዎቹ የነዚያ ጨቋኝ ሥርዓቶች አገልጋዮች ነበሩ። ባገራችን ስናየው ምንም እነኳን አገልጋዮቹ ያማርኛ ተናጋሪዎች በብዛት ቢኖሩበትም አማርኛን የተናገረና ሥርዓቱን ለማገልገል ዝግጁ የነበረ ሁሉ ተጠቃሚ የነበረበት ጊዜ ነው። ያማራ አገር የሚባለውን ቦታ ሁሉ በዚያን ጊዜ ዞሮ ያየ ህዝቡ ከሌላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ ባላነሰ መንገድ የተጎሳቀለ እንደነበር ይገነዘባል። ያገኘው ጥቅም ቢኖር ገገሮዎቹ በታሪካዊ አጋጣሚ አንድ አይነት ቋንቋ ስለሚናገሩ ብቻ የቋንቋና የባህል ጭቆና ሰለባ አለመሆኑ ነው።

ከላይ የተገለጸውን ሙሉ በሙሉ የማይቀበሉ እንዳሉ እገነዘባለሁ። የብሄር ጭቆና ያለ ጨቋኝ ብሄር አይኖርም የሚል የመከራከርያ ሃሳብ ያነሳሉ። እኔ ግን በጥልቀት ነገሮችን ካለመመርመር የተነሳ ድምዳሜ ነው ባይ ነኝ። ችግራችን እንደ ነጭና ጥቁር ጥርት ብሎ የሚታይ አይደለም። ውስብስብ ነው።

ይህንን ግንዛቤ ጠንቅቆ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው። ከየብሄሩ የመጡ የጥፋትና የመከፋፈል መልእክተኞች ይህን መሰረት አድርገው ነው ሰላምና አንድነት እንዲጠማን የሚያደረጉን ያሉት። የራሱን የወደደ ሁሉ የሌላውን የጠላ በማስመሰል ሰዎች ባህላቸውን ስላከበሩ፣ ቋንቋቸውን ሰላዳበሩና በዚያም ስለተማሩበት አማራንና አማርኛን የተቃወሙ በማስመሰል የ ጥላቻ ዕርሾ የሚጠነስሱትን ሁሉ ቦታ ልናሳጣቸው ያስፈልጋል፣ ወጊዱ ልንላቸው፣ የተሳሳቱንም ልንረዳቸው ይገባል።

በሌላ በኩል ደግሞ ያማርኛ ቋንቋና ባህል በሌላው ላይ ጫና ስለነበረው ብቻ አማራ ጨቋኝ ነው የሚለውን ሃሳብ የሚያጠነጥኑትን የመግሰጽና ማስተማር ግዴታ አለብን። የሁለቱም ጽንፈኛ አስተሳሰቦች የመጨረሻ ውጤት አንድ ነው። ጥላቻን ማስፋፋት።

………………

**አድልዎ**

በመጀመርያ ከላይ የተጠቀሰውን አስተዳደር -ለተወሰኑ ክልሎች አድልዎ ያደርጋል- በሚል የሚቃወሙትን አይተን እንለፍ። ይህ ነገር እውነትነት ካለው ገለልተኛ አካል ሊመለከተውና ሊታረም የሚገባ ነገር ነው። በዚህ ነገር በብዛት የሚታማው የትግራይ ክልል ስለሆነ በኔ በኩል ይህንን ነገር የሚያጣራ አካል ቢፈጠር የዚህ አባባል መነሸው ምንድነው ለሚለው ጥርት ያለ ሥዕል እነዲኖረን ያደርጋል ሚል ግምት አለኝ። ይህ አካል በክልሉ የሚታየው እድገት (ከሌላው



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የበለጠ ከሆነ) ያድልዎ ውጤት ነው ወይስ ህዘቡ ባካባቢው ኢነሸስት ሰለሚያደርግ? መነግስታዊ ያለሆኑ ክልል-በቀል ድርጅቶች በ እድገት ነክ እንቅስቃሴዎች ስለተሰማሩ? - የተጎዳ ክልል ስለሆነ ድጎማ ስላሰፈለገው? -ይህ ሁሉ መታየት ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል። በፌደራል ደረጃ ያለው የድጎማ ወይም የበጀት አመዳደብ በግልጽ የሚታወቅ ስለሆነ ነገሩን ማጣራት የሚያስቸግር ጉዳይ አይሆንም። የዚህ ጥያቄ መልስ በብዛት በጥላቻ ጎራ ተሰልፈው ያሉትን ሀይሎች ሰሚ ያሳጣል።

በሌላ በኩል የትግራይን ክልል በሚመለከት አንድ ነገር ጠንቅቆ ማወቅ የግድ ያስፈልጋል። መሬቱ በጣም የተጎዳ ነው። እጅግ ከመጎዳቱ የተነሳ አነዳንድ ቦታዎች ገበሬዎች አፈር ራቅ ካለ ቦታ ተሸክመው አምጥተው አዝርእት የሚዘሩበት ሁኔታ ነበር። ይህን አስከፊ ያነድ ዜጋ ህይወት መለወጥ የማነኛውም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው። ማንም እንደዚህ ዓይነቱን ችግር አይቶ ችላ የሚል መንግሥት ሃላፊነት የሌለው መንግሥት ነው። እንደሚመስለኝ ይህ የኢህአዴግ መንግሥት ለትግራይ ህዝብም ሆነ ለሌሎች ተመሳሳይና ልዩ ችግር ላለባቸው አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ካልሰጠ ተጠያቂ መሆኑን ማወቅ የሚኖርበት ይመስለኛል።

-----------------

<u>የ ክልል አስተዳደርና ኢትዮጵያዊነት</u>

ለውይይት እነዲያመች እነጂ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ተቃራኒ ናቸው ማለቴ አይደለም። ለሁሉም ሌላው ሰጋት ኢነዲህ የሚል ነው፦

**አገሪቱን በብሄር የሚከፋፍል ፌዳራሊስት አገዛዘ መሰረተ።**

- **በዚህም የተነሳ ያነዱ ብሄር ተወላጅ ሌላ ክልል ዉስጥ ሄዶ መስራት አልቻለም፤ መድልዎ ይደረግበታል ወይም ለመድልዎ በር ከፈቷል**
- **አለመተማመንንና መጠራጠርን ፈጥሯል፤**
- **ለወደፊቱ አንዲት ጠንካራ ኢትዮጵያ እንዳትገነባ የሚያደርግ ደነቃራ አስተዳደር ነው፥**

ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ስለወደፊቱ አነድነታችንና ህበረታችን ከሚቆረቆሩ ያለፈውን ጨቋኝን ከፋፋይ ያገዛዝ ስርአት ግን አጥብቀው ከሚገነዘቡ ኢትዮጵያውያን አካባቢም ጭምር የሚነሳ ጥያቄ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች በጥሞናና በስፋት ሊታዩ ይገባቸዋል።

እኔ የምመለከተው ከዘህ በታች እንዳለው ነው።

መቸም እንደሚገባኝ ማንም ኢትዮጵያዊ ያገሩን እድገት ይመኛል - ይፈልጋል። አንዱ ብሄር አልፎለት ሌላኛው ድሃ ሆኖ እድገት እንደማይኖር ደግሞ የሚገነዘብ ይመስለኛል። ካልሆነም ሊገነዘብ ይገባዋል። አነዱ አልፎለት አነዱ ተበድሎ በሰላም መኖር እነደማይቻል ያለፉ የተለያዩ አገሮችና የኢትዮጵያ ታሪኮች ለዚህ ምስክሮች ናቸው።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ዕድገት ደግሞ ያለ አንድነት ስሜት፣ ያለህበረት፣ ያለመከባበር፣ ያለእኩልነት መንፈስ የሚመጣ ክስተት (ፌኖሚነን) አይደለም። ስለዚህም የክልል በብሄር ብቻ አደረጃጀት ከነዚህ እሴቶች ጋር ያለው ተቃራኒነት ወይም አለመግባባት ምንድነው? እነዚህ ግንዛቤዎች ከስሜታዊነት በመነሳት የሚነገሩ ናቸው ወይስ በማስረጃነት (ታሪካዊ ይሁን ወይም አሁን በተጨባጭ የሚታይ) የሚቀርብ ነገር አለ? ልዩነቶቹ የሚታረቁ ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች በኔ ግምት በብዛት ከሚነሱት ጥቂቶቹ ናቸው።

…………………………..

ከስሜት ፈልቀው የሰው አእምሮ ነፍስ ዘርቶባቸው **"ወደ ዕውነትነት"** የተቀየሩ (ፐርሲቨድ) የሆኑና በተጨባጭ የሚታዩ ችግሮች ባንድ ላይ ሆነው መፍትሂውን ለመሻት የምናደርገውን ሙከራ ማደብዘዛቸው አልቀረም።

ተጨባጩን ስንመለከት ክልል አመሰራረት ላይ የማያስማሙ ችግሮች እንደሚኖሩ የሚያጠራጠር አይደለም። ከዚህ አንጻር የነበረውንና ያለውን ችግር ገዢው ፓርቲም ቢሆን እንደሚገነዘበው እርግጠኛ ነኝ። ይህ አንዱ ችግር ነው። ህዝቦች ለዘመናት አብረው በኖሩባት አገር ጥርት ያለ በብሄርና ብሄረ-ሰብ ላይ የተመሰረተ ክልል ማካለል በጣም አዳጋች ነው። በመጠኑም ቢሆን ችግር ይፈጠራል።

ሌላውና ዋነኛው የሚመስለኝ የብሄር-ክልል ችግር መብትና-ግዴታ ማወቅና-አለማወቅ ችግር ነው። በዚህም የተነሳ የክልል አሰተዳደሮች ከክልሉ ውጭ የሆኑትን ዜጎች መብት የመጋፋት ችግር ሊኖር መቻሉ ነው። ይህ ችግር በብዛት በተለይ በ ኦሮሚያና ባነዳነድ ደቡብ ክፍሎች ጎልተው እንደታዩ አንዳንድ ሰዎች ይናገራሉ። እንዲህ ዓይነቱ ክስተት (እውነትነት ካለው) ቢያንስ በአራት መንገድ ሊታይ ይችላል፦

1) **ግብዝ የሆኑ ሰዎች የድሮ 'ብድር' የመለሱ እየመሰላቸው የሚወስዱት የበቀል እርምጃ፣**
2) **አጋጣሚውን ተጠቅመው ራሳቸውን ለመጥቀም የተዘጋጁ ሙሰኞች በሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ ለዚህም ሲሉ ህዝብን ከማጋጨት ወደኋላ የማይሉ**
3) **ፌደራላዊ አስተዳደር ምን እነደሆነ ባለማወቅና ሥርዓቱ ሥር እስኪሰድ የሚፈጠረው ችግር (ግሮዊንግ ፔይንስ)**
4) **ወይም ሰዎች ከራሳቸው ግምትና እምነት ተነስተው የሚያወሩት ነገር**

እነዚህ ችግሮች እንደየክብደታቸው እየታዩ በጊዜ ካልተፈቱ ለወደፊቱ ችግር እንደሚያመጡ መታወቅ ይኖርበታል። ይህ የተባለው ችግር የደረሰው አሰተዳደሩ ሲሰተሚክ (መሰረታዊ) የሆነ፣ ሆን ተብሎ የተደነገገ ያድልዎ ችግር ስላለ ነው ወይስ ካሰራር ጋር የተያያዘ ችግር ነው?

…………………

ከዚህ በመለስ አንዳንድ አገር-በቀል ፓርቲዎች የሚያነሱት ትልቅ ነጥብ ጊዜ ሰጥተን ልናየው የሚገባ ነገር አለ። ይኸውም የብሄሮችን መብት ለማረጋገጥ በቋንቋ ብቻ መከለል የለበትም፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ/ጂዮግራፊያዊ አቀማመጦችንም አብሮ ማየት ያሰፈልጋል የሚለው ነው። በተጨማሪም በክልል መታገቱ ብሄሮች



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ውስጠ-ተኮር (ኢንዎረድ ሉኪንግ) ይሆናሉ፡ የ ኢትዮጵያዊነት ሰሜት እየላላ ይመጣና ያገር አንድነት አደጋ ላይ ይወድቃል የሚል ትልቅ ነጥብ አብሮ ይነሳል።

በጥሞና ላየው ይህ ፍራቻ መልስ የሚያስፈልገው፣ ሁሉም ሊያጠናው የሚገባና የጋራ መፍትሔ የሚሻ ነው። '**ኢትዮጵያዊነት**' እኛ ብቻ ነን የሚሉ ሰዎች በብዛት ደጋግመው ሰላነሱት ብቻ ችላ ልንለው አይገባም። እንዳውም ከሁሉም ይልቅ ባገኙት ክልላዊ መብት የተጠቀሙ ክፍሎች ጉዳዩ ይመለከታቸዋል። መብታቸው ተጠብቆ የሚኖረው ይህ አሁን የመሰረቱት የፌደራል ስርዓት ጠንካራ ኢትዮጵያዊነት ሰሜት ሲኖረው፡ የህብረ-ብሄር መለዮው ጎልቶ ሲወጣ ነው።

ያንድነት ሰሜትን የሚያዳብር ጠንካራ ፌደራላዊ መንግሥት ከሌለ ክልላዊ መንግስቶች የተረጋጉና የነዋሪውን ጥቅም አስጠባቂ ሊሆኑ አይችሉም። ያንድነት ሰንሰለቱ ካልጠነከረ ማዕከላዊ ፌደራላዊ አስተዳደሩ ያመጣው አዎንታዊ ለውጥ ዘላቂነት ላይኖረው ይችላል። ለዚህ ነው ከማንኛውም ቡድን በላይ ክልሎች ስለ ኢትዮጵያዊነት መጎለበት የበለጠ ተቆርቋሪነት አላቸው ያልኩት።

<u>IV</u>

<u>**ወደፊት እንዴት እንጓዛለን?**</u>

መንደርደርያ ይሆን ዘንድ ከዚህ በታች የሚመስሉኝን ባጭሩ ላቅርብ።

**በመጀመርያ ደረጃ** ሁላችንም በ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ ያገባናል የምንለው ሁሉ -ከሊቁ እስከ ደቂቁ- ራሳችንን መመርመር ተቀዳሚ ተግባራችን እናድርገው። ግንፍልነት፣ ቁጡነት፣ ማግለል፣ ካለኔ ዕውቀት ላሳር ማለትን፣ ኩራት የ ዕውቀት ሳይሆን የድንቁርናና የ ዕኩይነት መገለጫዎች መሆናቸውን አውቀን ራሳችንን ከነዚህ መገለጫዎች ለማራቅ ተግተን መነሳት አለብን። ይህንን ስል አንባቢውን በሙሉ ባነድ ብሩሽ እንደቀባሁት ተደርጎ እነዳይወሰድብኝ እጠይቃለሁ።

በሽታችንን ማወቅ ግን ተገቢና ተቀዳሚ መሆኑን ሁላችንም ተገንዝበን ማለፍ አለብን። ንቀቱ፣ ኩራቱ፣ ጥላቻው፣ አለመደማመጡ፣ ዓቅምን አለማወቁ አሁን ያለንበት የፖለቲካ ውዥንብር ውስጥ አስገብቶን እንዳለፈ መገንዘብ ተገቢ ነው። በገዢው ፓርቲና በተለይም በውጭ ዳያስፖራ ፖለቲከኞች መፋጠጥ ዋና ምክንያቶቹ እነዚህ ኋላቀር አስተሳሰቦች ናቸው ብየ አምናለሁ።

………………

ይህን ካልን ዘንድ ወደ ዋናው ቁምነገር እናዝግም።

አህአዴግ የብሄር ክልል የ እኩልነትን ሰሜት ያሰርፃል፣ ይህ ሰሜት ደግሞ አገራዊ አንድነትን ይመሰርታል ይላል። ተቃዋሚው ደግሞ ውስጠ-ተኮር ይሆንና የ ኢትዮጵያዊነት ሰሜትን ያቀዘቅዛል፣ የጋራ እሴቶች እንዲቀጭጩ ያደርጋል ብለው ይሞግታሉ። ሁለቱም ዕውነትነት አላቸው የሚል እሰተያየት አለኝ። ስለዚህም ሁለቱም ሃሳቦች የሚጣጣሙበት መንገድ መኖር ይኖርበታል። ቀደም ብለን እንዳልነው ዓንድነት የሁለም የ ኢትዮጵያ ህዝብ አጀንዳና ፍላጎት እንጂ አንዱ ወገን የሚያራምደው ሃሳብ አይደለም። ስለዚህም እንኳን ጦር ሊያማዝዝ ይቅርና ለያከራርፍ እንኳን የሚችል ጉዳይ መሆን አልነበረበትም።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ችግሩ በነዚህ ሁለት ያስተሳብ ዘርፎች መካከል የተሰነጉት የተለያየ ቀለም ያላቸው አክራሪ አሉታዊ ሃይሎች ናቸው። አክራሪነት በተፈጠሮው ወደመበጠስ ነውነ'ጂ ወደ ማጠናከርና መገንባት አያመራም። በኛ አገር ሲታይ አንዱ አክራሪ የብሄር መብት ተከራካሪ ሌላኛው ያንዲት ኢትዮጵያ ጋሻ-ጃግሬ ሆነው ግራ-ቀኝ ያምሱታል። ባሁኑ ጊዜ ደግሞ የ ሚያሳዝነውና የሚገርመው ሁለቱም አጽናፎች ላለው ገዢ ፓርቲ ጥላቻ ስላላቸው ብቻ ባንድ ጎራ ሊመሸጉ ይጥራሉ። እንዳው ተሳክቶላቸው የጋራ ዒላማቸው ከጠፋ ግን ይህችን አገር ምን እንደሚያስመስሏት መገመት አያስቸግርም።

በሌላ በኩል ደግሞ ገዢው ፓርቲ ያክራሪዎች ጋጋታ ስላሰቸገረው ይመስላል ደግ በሚያስቡት ላይ ሳይቀር ጥርጣሬና አንዳንዴም የሃይል እርምጃ በመውሰድ ነገሩን በማብረድ ረገድ አሉታዊ አስተዋጽኦ ማድረጉ አልቀረም።

<u>V</u>

## <u>*መንደርደርያ የመፍትሄ ሃሳቦች*</u>

1. *መፍትሄው እንደሚመስለኝ ህዝቡ ነው።*
   *ኢህአዴግ እኩልነት ዓነድነትን ያጠናክራል ሲል እውነትነት አለው። ስለዚህም የቆየውን የብሄሮች ጭቆና ለማስወገድ ሲል የብሄር አስተዳደር መስርቷል። ህዝባዊ አገዛዝ ማጎለበት (ኢመፓወርመንት) ማለት ካነስተኛ ወረዳ (ግራስ-ሩት) ጀምሮ የህዝብ ስለጣን ማስረጽ ነው። ሃይልና ስለጣን ተግባራዊ የሚሆነው በክልል (ሰፔስ) ነውና ኢህአዴግ ክልል መመስረቱ ባጠቃላይ ትክክል ነው ብዬ አምናለሁኝ።*

   *ባንጻሩ ደግሞ እንዲህ አይነቱ አስተዳደር ልዩ ትኩረት ካልተሰጠው ዓላማዉን ስቶ አገራዊነትን ችላ በማለት ክልላዊነትን ሊያበረታታ እንደሚችል እንገነዘባለን። ሁለቱንም ማጣጣም የሁላችንም ጥቅም ማሰጠበቅ ስለሚሆን ብዙ ሊያከራክረን የሚገባ ጉዳይ አይመስለኝም። አሁን ያለው ፌደራል ሲሰተም ለክልሎች የሚገባውን ያህል መብት አይሰጥም የሚል አስተሳሰብ ባንድ በኩል፣ አይ! በጣም ልልና የማዕከላዊውን መንግሥት እጅ የሚያስር በጣም ልቅ ነው የሚሉ ሃሳቦች በሌላ በኩል ሆነው ሲያስተጋቡ እንሰማለን። ሚዛኑ የት ነው ያለው?*

   *ስለዚህም በኔ ዕይታ መነግስትና ተቃዋሚዎች፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ወኪሎች፣ አዋቂዎች/ ምሁራን የተስማሙበት ልዩ ኮሚሺን ተቋቁሞ የህዝቡ ስሜት ምን እንደሆነና ችግሩ እነዴት ሊፈታ እነደሚችል መጠናት ያለበት ይመስለኛል። ከህዝቡ የሚመነጩ መፍትሄዎች ባለቤትነት ስለሚኖራቸው ዘላቂነታቸው ይረጋገጣል።*

2. *ቋንቋንና ፊደልን አስመልክቶ አሁን ያለውን ፖሊሲ በጋራ መመርመር።*
   *ቋንቋ ህዝብን እንደሸረሪት ድር የሚያስተሳስር መሣሪያ ነው። ስለዚህም*



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የጋራ ቋንቋችን የ ሚያድግበትንና ሁሉም ዜጋ የሚግባበትን መንገድ ልንፈልግ ይገባል። ይህ ማለት ግን ሌሎች የተለያዩ ብሔር ቋንቋዎች ወደ ጎን ይተዋሉ ማለት አይሆንም።

የቋንቋቻችን ዕድገት የሁላችንም ጉዳይ መሆን አለበት። ከንግዲህ ታዳጊ ኢትዮጵያውያን ባንድ የ ኢትዮጵያ ቋንቋ ብቻ ተወስነው ማደግ የለባቸውም። ለሌላው ብለው ሳይሆን ለራሳቸው የወደፊት ግላዊ (ኢንዲቪጁል) ዕድገት ሲሉ፣ ለ ኢትዮጵያዊነት ስሜት፣ ላነድነት ሲሉ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ሄጄ በነበረበት ወቅት ከትንሹ ወንድሜ ጋር የደረግኩት ውይይት ትዝ ይለኛል። ገና መዋእለ-ህፃናትና (ኪነደርጋረተን) አንደኛ ክፍል የነበሩ ልጆቹን ሌላ ቋነቋ - የኦሮምኛ ቋንቋ ያስተምራቸው እንደሆነ ጠየቅሁት። ነገሩ በጭራሽ ጭንቅላቱ ውስጥ እንዳልነበረ ተገንዝቤ ብጠይቀው ትምህርቱም እነደማይሰጥ ነገረኝ። ይህ ነገር መቀየር ይኖርበታል። በተለይ የሰዉ አስተሳሰብ።

በዚህ አኳያ ስናየው የ ኢትዮጵያ ፌደራልና የክልል መንግሥስቶች ተጨባጭ እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል የሚል ዕምነት አለኝ። እነደሚመስለኝ መንግሰቶች ከክልሉ ቋንቋ በተጨማሪ አንድ ወይም ሁለት ሌላ ቋንቋዎች በግዴታ ልጆች እንዲማሩ ማድረግ መጀመር አለባቸው። እየተደረገም ከሆነ እሰየው!! እውቀቱ -ላገሪቱና ለተማረው-እጅግ ጠቃሚነት እንዳለው ሁሉም የሚረዳው ስለሆነ ለምን የሚለውን ጥያቄ ሳልዳስሰው አልፋልሁኝ።

3. በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች 'አንዲት ኢትዮጵያ'፣ 'ጠንካራ ኢትዮጵያ' የሚሉ ቃላቶች ተደጋግመው ተነስተዋል። እነዚህ አባባሎች ምንን ነው የሚያመላክቱት? ንጹህ የሆነ ያንድነት ፍላጎት፣ የወዳጅነት አባባል ነው ወይስ ያለፈውን ስርዓት ከሚናፍቁ አንድ ቋንቋ፡ አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ማዕከላዊ አገዛዝ እንዲኖር ከሚፈልጉ አካባቢዎች የሚነገር ውስጠ-ሚሰጢር (undercurrent) ያለው አባባል ነው? ይህንን ጠንቅቆ ማወቅ የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ አንፃር ሲታይ ጠቃሚነት አለው። ጠንካራ ኢትዮጵያ የሁሉም አጀንዳ መሆኑን የሚያሳይ ጥናት ማካሄድ፡ ኢትዮጵያ ከንግዲህ የብሄር-ብሄረሰቦችን ጥቅምና ፈላጎት ከሚያካትት የፌደራል ሰርዓት ሌላ አማራጭ እንደሌለ የማሳወቅ ሃላፊነት ምሁሩ ኢትዮጵያዊ መጀመርያ ለራሱ ቢረዳው ቀጥሎም ሌላውን ቢያስተምር ትልቅ ሚና የመጫወት ዕድል ያገኛል የሚል እምነት አለኝ። ይህን ማለት ያሰገደደኝ ሰለ አንድነትና 'ጠንካራ' ኢትዮጵያ ብበዛት ከጥላቻ ፖለቲካ ጎራ ሲስተጋባ መስማቴ ነው።

4. ሌላው ዋናው ትልቁ ሥራ ጥላቻንና መናናቅን መታገል ነው ብየ አምናለሁኝ። ይህንን እውን ለማድረግ ከተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌላ የህብረተ-ሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ወገኖች የሚገኙበት ቡድን ማቋቋም አሰፈላጊ ነው ብየ አምናለሁኝ። ዋናው ስራውና አላማው ያገር አንድነትንና የብሄር-ብሄረሰቦችን መከባበር ማራመድ ሲሆን ብሄር-ብሄረሰቦች እኩልነትን በተጨባጭ እንዲከበር ማደረግ ነው።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

በተለይ ያገር ሽማግሌዎች የሚገኙበት ይህ ተቋም በ ኢትዮጵያውያን መካከል ተጨባጭና አይመሯዊ ዕርቅ እንዲኖር፣ ሕግን ያላከበረ የፖለቲካ ተቀናቃኝ ሁሉ መንግሰታዊ ይቅርታ እንዲያገኝ ማድረግ፡ መሸምገል የመሳሰሉትን የሚያካትት ቢሆን ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

አንባቢ እንደሚገነዘበው እነዚህ ድፍን ሃሳቦች መብላላት እንዳለባቸው እገምታለሁ። ለውይይት እንዲያመቹ ተብለው በግርድፉ ተቀምተዋል። አንባቢዎች ከዚህ ተነስተው የሃሳቦቹን ይዘቶች እነዲመረምሩ እጋብዛለሁኝ።

----------------

VI

***መደምደመያ***

ችግሮቻችን አያሌ ናቸው። በዚህ ጽሁፌ ባንዱና ዋነኛ በመሰለኝ ላይ የሚመስለኝን ጽፌያለሁ።ታዳጊና ገና ለኛ የሚሆነውን የዲሞክራሲ ዓይነት ለመመስረት (አዎን! ገና ለኛ ስለሚሆነው ዲሞክራሲ ወይይት ያስፈልገናል!!) በምንዳክርበት በነዚህ ዓሥርት አመታት በችግሮቻችን መብዛት ብዙም ልንገረምበት የሚገባ አይመስለኝም።

በርግጥ ባህላችን ለ እድገታችን በመጠኑም ቢሆን ልጓም እንደሆነብን እየተገነዘብን የመጣን ይመስለኛል። ትዕግሥስትና መደማመጥ በባህላችን ገና ብዙ ይቀረዋል።

በ ኢትዮጵያ እጅግ የሚያስደስት የ ኤኮኖሚ ዕድገት እያየን አንዳንድ ቡድኖች ይህ እድገት እውን የሆነው በሚጠሉት መንግሥት አመካኝነት ስለሆነ ብቻ ለያጥላሉትይሞክራሉ። አንዳነዶቹም ውሸት ነው ብለው ደፍረው ይናገራሉ። ያለው መንግሥት እንዲወድቅ ስለተፈለገ ብቻ የሶማሌን ጠረኛ ፀረ-ሰላም ሃይል ይደግፋሉ፣ ከኤርትራው አቶ ኢሳያስ ጋር ያብራሉ።

የ ኢህአዴግን መንግሥት ለማጥለላት ሲባል ላገሪቱ መጥፎን ነገር መመኘት አስደንጋጭ ነገር ነው። ገና ፍርፋሪ ይደርሰናል ተብሎ አገሪቱን ላራዊቶች መዳረግ ብልህነትን አያሳይም። አራዊቶች ከነገሱ ፍርፋሬ አይገኝም። የትላለቅ አራዊቶች አገልጋይ -ትናነሽ አራዊቶች ለመሆን ካለተመረጠ በስተቀር።

ይህ ነገር ቶሎ ይቁም። አህአዴግም፡ ኢዴፓም፣ኦፍዴንም፣ ቅንጅትም፣ ህብረትም፤ ሁሉም ለ ኢትዮጵያ ደጉን የሚያስቡ ድርጅቶች ናቸው። አካሔዳቸው ላይ ይለያያሉ። ይህ ያለ ነገር ነው። ግን ልዩነቱ በጨዋነትና በመከባበር መፈታት ይኖርበታል።

ሰሞኑን ጥሩ ነገር እያየን ነው። የ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለፖለቲካ እስረኞች ፍርድ እየሰጠ ነው። አንዳነዶቹም እየተፈቱ እንደሆን እንሰማለን። ተጣራጣሪዎች ይህንን ሂደት የማስመሰል ሂደት ብለው ሊያጥላሉት ይሞክሩ ይሆናል። ለኔ ግን ብዛት ያላቸው ሰዎች መፈታት እንደ ተጨባጭ ገለልተኛነት እንዳየው ህሊናየ ያስገድደኛል። የተፈቱት ሰዎች ናቸው፤ በነዚህ



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ሰዎች ህይወት አነፃር ስንመለከተው መፈታታቸው ትልቅ ለውጥ በህይወታቸው ላይ ያመጣል። በኔ አመለካከት ይህ ተጨባች አዎነታዊ ለውጥ ነው መለኪያችን መሆን የሚገባው።

ይህ ጥሩ ጅምር ይቀጥል ዘንድ ሁላችንም ገንቢ ሚና ብንጫወት አገራችን በሁሉም ዘርፍ ታድጋለች። በዚህ እርግጠኞች እንሁን።

....................

አብዛኛው የዚህ ጸሁፍ ትንታኔ የሚመለከተው የ ኢትዮጵያ ዳያስፖራን ነውና ስለኛ ዲያስፖራዎች ትንሽ ልበልና ነገሬን ልቋጭ። ዕጅግ አበዛኛው የኛ ሰው ውጭ አገር የሚኖረው ራሱን ለመርዳት ሲል፣ ለራሱ ምቾት ሲል ነው። ምንም እንኳ ላወጣጡ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም። ስለዚህም ግትርና መንቻካ የፖለቲካ አቋም ወይም አስተሳሰብ የለውም። መንቻካው ፖለተካ የሚጠነጠነው (በብዛት) የራሳቸው የግል አጀንዳና ችግር ያላቸው፣ ካለው ገዢ ፓርቲ ጋር በጣም ጥቂቶቹ ደግሞ ከ ኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ባንድ ይሁን በሌላ ምክንያት የማይታረቅ ጠብ ውስጥ የገቡ ናቸው። እኒህ ጥቂቶች ያለ የሌለ ሓይላቸውን ተጠቅመው ሌት ተቀን በፖለቲካው አለም ስለተሰማሩ (ሌላ ምርጫ የሌላቸው ስለሚመስላቸው) ሌላውን አገራዊ ፖለቲካ ከግል ጥቅማቸው ጋር በማዛመድ የመሪነቱን ልጓም ጨብጠዋል። አፀያፊ ቋንቋና ዘዴ ስለሚጠቀሙም አብዛኛው ስደተኛ (የውጭ ነዋሪ) ከነሱ ጋር አለመጋፈጥን ይመርጣል። ይህ ነው የዳያስፖራ ፖለቲካ ዋናው መልኩ።

ታድያ ምን ይበጃል? እንደኔ ፈላጎትና እይታ ቢሆን አጭሩና የቁርጡ መልስ ዳያስፖራው በ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የመሪነት ሚና ለመጫወት የሚያደርገውን ሙከራ ማቆም አለበት ነው። ለውጥ፣ ያሰተዳደር ለውጥ እነደሽቀጥ ከውጭ አይላክም። ይክፋም ይበጅም አገር ውስጥ ያሉ ፓርቲዎች -ገዢው ይሁን ተቃዋሚው- ናቸው ያገሪቱን ዕድል ከህዝቡ ጋራ ሆነው የሚወስኑት። እኛ ውጨኞቹ በሚመስለን የፖለቲካ ዘርፍ ዕይታ ተመርኩዘን የውስጠኞቹን መርዳት፣ ላገራችን የሚበጀውን ማድረግ፣ በ ኤኮኖሚው መስክ ተሰማርተን አገራችንንና ራሳችንን መረዳት ነው የሚጠበቅብን።

አለበለዚያ ሁኔታዎች በቅጽበት በሚለዋወጡበት አገር፣ የድሮዋን ኢትዮጵያ ምስል በጭንቅላታችን ላይ ቀርፀን የምናደርገው እንቅስቃሴ አገራችንን ከመጉዳት ራሳችንን ደግሞ ለ ዓይምሮ መታወክ ከመዳረግ በስተቀር የምንፈይደው ነገር አይኖርም።

በትንሹ እንጀምር። ውጭ ሆነው መጥፎውን ብቻ የሚያወሩትን ወገኖቻችንን ደግኑም እንዲዳስሱ እናበረታታቸው። ያገር አጀንዳ ከግል አጀንዳ ጋር አያገናኙት። ላገሪቱ እድገት ተጨባች አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችሉ መንገዱን እናሳያቸው።

ስለዚህም የዲያስፖራ ፖለቲከኛው ስም ማጉደፉን፣ የሰዎች ዝርዝር ስም እያወጡ የግለሰቦችን ስነ-ሰውነት/ ተክለ-ሰውነት/ መግደሉን (ካራክተር አሳሲኔሽን) ያቁም። ፖልቲካውን ትቶ በግለሰብ ላይ ያተኮረ ውርጂብኝ አፀያፊ ነው። ከብልግናም በላይ ነው። ጨዋ 'ኢትዮጵያዊ' ባህልና ስነ-ምግባር አይደለም።



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

የኢትዮጵያ መንግሥትም ይህን ያገራዊነት ስሜትን ያበረታታ። ሆደ-ሰፊ ይሁን። የሌሎቹን ጥፋት ይቅር ካለ ሌሎቹም የሱን ጥፋት ይቅር ይሉለታል። ያለፈው አልፏል አሁን አዲስ ምዕራፍ ተከፍቷልና ኑ ! አብረን እንገንዘ የሚል ጥሪውን ያስተላልፍ። ያነድነት ሀረጉ ይጠንክር። አዲሱን የ ኢትዮጵያ ሚሊኒየም በተጨባጭ የለውጥ ዘመን የምናደርገው ራሳችንን ስንለውጥ፡ መጀመርያ ከራሳችን ጋር ለጥቆም ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ያላንዳች ቅድመ-ሁኔታ ዕርቅ ስናደርግ ነው።

አዎን!

**"የኢትዮጵያ ሚለንየም የ ኢትዮጵያ ሕዳሴ ይሁን"**



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com